## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የአርብ ፕሮግራም

የአርብ ፕሮግራም የምጸልይበት፣ የምንንቃቃበትና የምንማርበት ፕሮግራም ነው። የምንችል ሁሉ እንድንካፈል እናበረታታለን። ጌታ ይባርካችሁ!

### ስለ አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ሰምተዋል?

1) እግዚአብሔር ስለሚያፈቅረን ለሕወታችን አስደናቂ እቅድ ሰጥቶናል።

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐንስ 3፡16

2) ሰው ኃጢአተኛ የሆነ ባህርይ ስላለውና በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ስለ ተለየ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ፍቅርና እቅድ ሊለማመድ አይችልም።

"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።" ሮሜ 3፡23

3) ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ በመሞቱ በእርሱ በኩል ብቻ ሰው ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል።

"እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" ዮሐንስ 14፡6

4) ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችንና ጌታችን አድርገን በመቀበል እግዚአብሔር አምላክ ለኛ ያለውን ፍቅርና እቅድ ልናውቅና ልንለማመድ እንችላለን።

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" ዮሐንስ 1፡12

*"በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፥ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።" (ኢሳ. 27፡6)*



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**


ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| | |
|---|---|
| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | Chicago Yemsrach Evangelical Church |

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




## "ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው።"

(መዝ. 119፡105)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**July 30, 2017**

**ሐምሌ 23፤ 2009 ዓ.ም.**

## የእለቱ ፕሮግራም መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | እህት ሰናይት ከበደ |
| አምልኮ....................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም  ብረሃኑ አንበሴ |
| ቃል ............................ | ፓስተር ዶ/ር ቤዛለም ፍስሃ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"ሁላችን የእግዚያብሄርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘ አንድነት ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመስራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።" (ኤፌ. 4፡12)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 6602 N. Damen Ave., Chicago IL 60626 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ማክሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ  ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ዴሌቦ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

## <u>አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች ፱ -- አስተማሪዎች</u>

*"እርሱም ... ሌሎቹም ... አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ።" (ኤፌ. 4፡ 11)*

አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያስተምሩ ናቸው። ከዚህም የተነሳ በቤተ ክርስቲያን ሚዛን የጠበቀ እድገት እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጾ ያደርጋሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታምራትና በድንቆች እንዲሁም በትንቢት መንፈስ ያገለገለ ሲሆን እንዲሁም ድንቅ አስተማሪም ነበር። ለዚህ ዋቢ ከተራራው ትምህርት የሚበልጥ የለም። ማቴዎስ ይህንን ክፍል ሲጀምር "አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው" ይለናል። (ማቴ. 5፡2) እንዲሁም ጌታችን በምሳሌ አፉን በመክፈት ሰዎች በሚገባቸው መልኩ ጥልቅ የሆኑ መንፈሳዊ ትምህርቶችን ያስተምር ነበር። እንዲሁም በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን አጵሎስ በማስተማር አገልግሎቱ የታወቀ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እርሱ በመጽሐፍት እውቀት የበረታ ነበር። እንዲሁም በመንፈስ እየተቃጠለ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ <u>በትክክል</u> ያስተምር ነበር። (ሐዋ. 18፡ 24-25) ስለዚም አገልግሎቱ ማጠጣት (ማለትም የዳኑት የሚድጉበትን ቃል በማስተማር) ነበር። (1ቆሮ. 3፡6) <u>የጌታ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሙላት እንድትመጣ ቅዱሳን በኃይልና በትንቢት አገልግሎት ብቻ ሳይሆን በትምህርትም መታነጽ ይኖርባቸዋል። ለዚህም ነው በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ነብያትና መምህራን የነበሩት።</u> ለመታነጽ ነብያትም አስተማሪዎችም (ሌሎቹም የአገልግሎት ስጦታዎች) ያስፈልጉናል። አንድ የአገልግሎት ስጦታ ብቻውን በቤተ ክርቲያን የተሟላ እድገት አያመጣም።

የአስተማሪዎች ዋንኛው ብቃት የጌታን ትምህርት በትክክል መረዳትና ለሌሎች ግልጽ በሆነ ሁኔታ ማስተማር ነው። ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸው ትምህርት ነበር። ስለዚህም የታላቁ ተልኮ ትዕዛዝ የጌታን ትምህርት ማስተማርን የሚጠቀልል ነው። ("እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ <u>ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው</u> ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" (ማቴ. 28፡ 19-20)) ሐዋሪያቱም ያስተምሩ የነበረው ከጌታ የተቀበሉትን ትምህርት ነበር። ስለዚህም ቃሉን የተቀበሉት በሐዋሪያት ትምህርት ይተጉ እንደነበር ተጽፏል። (ሐዋ. 2፡42) ስለሆነም አስተማሪ አስቀድም ለራሱ የጌታን ትምህርት በትክክል መረዳት ይኖርበታል። የትምህርት ስህተት በጣም አደገኛ ስለሆነ (እራስም ስቶ ሌሎችንም ለማሳት ምክንያት ይሆናልና) አስተማሪ የትምህርቱን ትክክለኛነት እርግጠኛ መሆን ይጠበቅበታል።

ሌላው የአስተማሪዎች ብቃት የተረዱትን የቃል እውነት በሚገባ መልኩ ለሌሎች ማስተላለፍ ነው። ስለዚህም ሐዋሪያው ጳውሎስ በመንፈስ ልጁ ለሆነው ለጢሞቲዎስ ሲጽፍለት "ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን <u>ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ</u> ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ" ይለዋል። (2ጢሞ. 2፡2) መንፈሳዊ መረዳት አንድ ጉዳይ ሲሆን የተረዱትን ማስተማር መቻል ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው።  ጌታ አስተማሪዎችን ያብዛልን። አሜን።